#ጊዜው_አሁን_ነው!
#ዕድል_አሁን_ነው!
•
ዛሬ በመጻሕፍ ዳሰሳ የምህረት ደበበ ሌላ ሰው መጻሕፍን ስለጊዜ ፍልስፍና ያስቀመጠውን ለመረዳት፣ ለመተንተን እንሞክራለን።

መጻሕፉ ገጽ 34 ላይ ስለጊዜ መነሻ የሚሆን ፅሁፍ ይጠቅሳል "ጊዜ እንደ ቦታ በወደዱት አቅጣጫ ሰንጥቀው የሚሄዱት ዕውነታ አይደለም። የጊዜ ላይ ጉዞ በተወሰነ ፍጥነት የአንድዮሽና የወደ ፊት ብቻ በመሆኑ ሰው የጊዜ እስረኛ ነው።"

በዚህ አንቀፅ በዋናነት ለመነገር የተፈለገው የሰው ልጅ የጊዜ እስረኛ መሆኑን ነው። በትክክልም ሰው በጊዜ ግዞት ውስጥ የሚኖር አሳዛኝ ፍጡር ነው። መለወጥ፣ ወደ ኋላ መጎተት፣ ወደ ፊት መሳብ ከቶውንም አይቻለውም። ግን ሰው ጊዜን ሊቀድም ይሮጣል። የሰው ልጅ ህልው ከሆነ ጀምሮ ጊዜ መቁጠሩን አሃዱ አለ። (እዚህ ጋር ለማለት የፈለኩት ምናልባት ጊዜ ሰው ሳይፈጠር ጀምሮ የነበር ሊሆን ይችላል። ግን አዳም ሳይፈጠር የነበረው የጊዜ መቁጠሪያ ከአሁኑ ዓለም ጊዜ ጋር ተመሳሳይ አይሁን ምንም የሚታወቅ ነገር ባለመኖሩ በእርግጠኛነት ለመናገር ያዳግታል)። የጊዜ እሽክርክሪት ከሰው ልጅ ቁጥጥር ነዓ ነው። ም/ክ የሰው ልጅ ሟች ነው። ስለዚህ ሰው ህልው ሲሆን ውልድትና ሞትን በሕይወቱ ውስጥ ተካተተ። በዚሁ ሎጂክ ሕይወት የሰው ልጅ ውልደቱ ሲሆን ጊዜ ደግሞ የሰው ልጅ ሞቱ ነው። ሞት ዕድሜ እንጂ እንዴት ጊዜ ሊሆን ይችላል ሊባል ይችላል። ግን መረሳት የሌለበት ዕድሜ ራሱ የጊዜ ቁራሽ አካል ነው።

ከመጻሕፉ "ጊዜ የዘላለም አሽከር ሲሆን፣ ሰው ደግሞ የጊዜ ባሪያ ነው። ሰው ጊዜን በደቂቃ፣ በሰአት፣ በወራትና በዓመታት ሸንሽኖ፥ ከግድግዳው ሰቅሎ፥ በዕጹ ላይ ጠፍሮ ሊገዛው ሊቆጣጠረው ይሞክራል። ጊዜ ደግሞ ሰውን ከልጅነት ወደ ወጣትነት፣ ከጉልምስና ወደ ዕርጅና እያከለፈለፈ ከሞት ደጃፍ ያደርስና መቃብር ይጨምረዋል። በከረምትና በበጋ፣ በጸደይና በመጸው እየተመሰለ፣ መልኩን እየቀያየረ ሲመጣና ሲሄድ፣ ሲዞርና ሲፈራረቅ ... የጊዜ ጉዞ ያዙሪት እንጂ የወደፊት አይመስልም። በድል ፈረስ ላይ ተቆናጦ በስኬትና በውድቀት፣ በቀጠሮና በድንገት፣ በጥበቃና በጥድፊያ ተጠቅሞ የሰውን ዕጣ ፈንታ የሚወስን ጊዜ መሆኑን በቀላሉ እንዘነጋለን። ጊዜን መግዛት ሲባል ራስን እንጂ ጊዜን ማስገዛት አይደለም።"

ከላይ በትንታኔ እንዳነሳነው ጊዜ የተፈጠረው ውልደትና ሞት በመፈጠራቸው ነው። ውልደትና ሞት ባይኖሩ ኖሮ ጊዜ የሚባል ቀመር አይኖርም ነበር። ዘላለማዊ የሆነ አካል የጊዜ እስረኛ አይደለም። ስለዚህ አምላክ ጊዜን ለሰው ልጅ እንደፈጠረው መረዳት ይቻላል። ጊዜ ራሱን ችሎ የሚጓዝ ቢመስልም ህልው እንዲሆን የሰው ልጅ መኖርን ይሻል። ም/ክ መወለድና መሞት የሰው ልጅ ባህርያት ናቸው። ይሄም የዚህች ምድር መገለጫዎች ናቸው። ስለዚህ ጊዜ ሚኖረው ምድር ላይ ብቻ ነው።

የሰው ልጅ እጣ ፋንታ በዕጹ ላይ እንጂ በጊዜ ላይ አይደለችም። ሕይወት ምርጫ ነች። ሰው እጣ ፋንታውን በወደደው በፈቀደው የመከተብ ስልጣን ተሰጥቶታል። ይሄ ማለት ሰው በራሱ ላይ ጌታ ነው። ስለዚህ ሰው ጊዜን ለሞቆጣጠር ከመሞከር ይልቅ እጣ ፋንታውን (ዕድሉን) መቆጣጠር ይችላል።

#ከመጻሕፉ "በጊዜ ውስጥ ትናንት የትዝታ፣ ዛሬ ደግሞ የተስፋ ጎተራዎች ናቸው። ካመለጠ ትናንት ... ያልመጣ ነገ ይሻላል። በዕጅ ያለ ዛሬ ግን ከሁሉም ይበልጣል። ዛሬ ሁሌም ያለ እየመሰለ የማይደገም ... ተመልሶ የማይመጣ ... ላንድ አፍታ በቅጽበት ታይቶ ዳርቻ ከሌለው የዘላለም ጠፈር ገብቶ የሚሰወር ... በትናንትና በነገ መሃል የተሸነቆረ ዕንቁ ነው። የዛሬ ምስጢሩና ጉልበቱ ያለው ደግሞ አሁን ላይ ነው። ቅድምና በኋላ ግን ያለቦታቸው ዛሬ ውስጥ የተደነቀሩ የትናንትና የነገ ሽርፍራፊዎች ናቸው።"

ጊዜ የሶስት ዕውደቶች ጥርቅም ነው። ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገ። ትናነት ያለፈ፣ ዛሬ ያለ፣ ነገ ደግሞ ያላለፈ፥ የሚመጣ። ስለዚህ ሰው ዕድሉ ወይም እጣ ፋንታው በመዳፉ ስር ነች ካልን ስለዚህ በቁጡጡሩ ስር ያለው ዛሬ ነው። አስተውሉ ዛሬ ስል ጊዜን ማለቴ አይደለም እጣ ፋንታን እንጂ። ስለዚህ ከትናንት ዕድል የነገ ዕድል ይሻላል ግን የዛሬ ዕድል ግን ከሁሉ ትበልጣለች። በዛሬ ውስጥ ደግሞ ቅድም፣ አሁንና በኋላ ተሰድረው ይገኛሉ። ግን ቅድም የትናንት ልጅ ነች፣ በኋላ ደግሞ የነገ አባት ነው። ስለዚህ ዕድል (እጣፋንታ) አሁን ነች።

#ከመጻሕፉ "የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑ ጨቅላ ሕፃናት ካልተነካ ቱባ ዕድሜያቸው ላይ ብዙ ዛሬዎች መና ከዋሉ በስተመጨረሻ በጸጸት የተሞላ የዕርጅና ኩሊ መሆናቸው አይቀርም። የልጅነት ጨዋታ፣ የወጣትነት ፍቅር፣ የጉልምስና ስኬት፣ የዕርጅና ሞገስ በዋናነት የዛሬ

ዕድል ፍሬዎች እንጂ የነገ ተስፋ ወይም የትናንት ትዝታ ውጤቶች አይደሉም።"

ዕድሜ የጊዜ ቁራሽ አካል ነው። ጊዜ በመኖሩ ዕድሜ ይኖራል። ውልድትና ሞት ደግሞ የዕድሜ ርዝማኔ ነው። ዘላለማዊነት ውስጥ ዕድሜ እርባና ቢስ ነው። ጊዜም አይጠቅምም። የሰው ልጅ ሲወለድ ህፃን ምናልባት ሲሞት ህፃን፣ ወጣት፣ ጎልማሳ፣ ሽማግሌ ሊሆን ይችላል። በተለምዶ የዕድሜ ባለጠግነት የብዙ ዕድሜ ርዝማኔ እንደሆነ ይናገራል። ማለት የእድሜ ባለጠጎች ሽማግሌዎች ናቸው ሲባል የተለመደ ነው። ግን የዕድሜ ባለጠጎች ህፃናት ናቸው። ህፃናት ብዙ ያልተከተበበት የዛሬዎች ወይም የአሁኖች ስብስብ ሀብታሞች ናቸው። ሽማግሌዎች ግን ጥቂት ዛሬዎች ብቻ ነው ያሏቸው። ግን በሽምግልና ውስጥ ያለፉት ዛሬዎች ምናልባት በመልካም ቀለም ደምቀው ይሆናል። ሆኖም በዛው ልክ በመልካም ቀለም ያልደመቁትም ብዙ ናቸው። ሕፃናት ግን ሁሉም ዛሬዎቻቸው ነጭ ወረቀት ነው። ወላጆች ልጆችን በስነ ስርዓት ካሳደጓቸው ዛሬዎቻቸው በአብሪ ብርሃን ይንቦገቦጋል።

#ከመጻሕፉ "ጊዜ እንደ ቦታ ደርዘ ብዙ የሕይወት ዕውነታ ነው። ሐሳብ አንዱ በጊዜ ውስጥ ወዲያ ወዲህ የሚያጓጉዘን አውሮፕላን ነው። ሁለተኛው በጊዜ ውስጥ መንሸራሸሪያ አውሮፕላን ደግሞ ዕንቅልፍ መሆኑ ነው። ሰው በምናቡና በራዕዩ በጊዜ ውስጥ ወደ ፊት ይጓዛል። በትዝታውና በትውስታው ደግሞ ወደ ኋላ ሊጉድ ይችላል።"

ጊዜና ቦታ ከሚለያያቸው ውስጥ ጊዜ የአንድዮሽ አቅጣጫ ጉዞ ነው፣ ቦታ ግን የብዙዮሽ አቅጣጫ ጉዞ ነው። ማለትም ጊዜን ማሳበር አይቻልም ለምሳሌ ከቀኑ 6 ሰአት የሆነው ጊዜ አሳብረን/አቋርጠን ከምሽቱ 1 ሰአት ማድረግ አይቻለንም። ቦታ ግን ማሳበር ማቋረጥ ይቻላል። ስለዚህ ሰው በጊዜ ላይ የሚጓዘው አንድም በሀሳብ ነው አንድም ደግሞ በዕንቅልፍ ነው። በሀሳብ ስንመሰጥ ጊዜ በፈጥነት ይጓዛል። በተመሳሳይም ዕንቅልፍ ጊዜ በቀላሉ እንዲያጥር/እንዲያልፍ ያስችላል።

#ቸር_ጊዜ!
•
#በአንተነህ
#ቅዳሜ ግንቦት ፲፯ ቀን ፳፻፲፭